ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች

ሐምሌ 2009 ዓ.ም. ቁጥር 33

# በጫት ስራ ላይ የተሰማሩ ሕጻናትና ልጆች የትምሕርት ሁኔታ፡- የሁለት የጫት ንግድ ማዕከላት ምልከታ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ኃብዞ ያወያያል።

♣ ♣ ♣

በኣዲስ አበባ (ኤፍ. ኤም አዲስ 97.1 ሞገድ) እና በሻሸመኔ (ፋና ሻሸመኔ 103.4) ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

♣ ♣ ♣

ድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል።

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን።

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

## 1. መግቢያ

በተመራማሪዎች ዘንድ *ካታ ኢዱሊስ* (*Catha edulis*) እየተባለ የሚጠራው ጫት፤ ዓመቱን ሙሉ አረንጓዴ ሆኖ መቆየት የሚችል ተክል ነው። ኢትዮጵያ፤ የመን፣ ኬንያ፣ ዑጋንዳ፣ ማላዊና ደቡብ አፍሪካ ጫት በስፋት ከሚመርትባቸውና ጥቅም ላይ ከሚውልባቸው ሀገራት ጥቂቶቹ ናቸው። የጫት ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙዎች ከሚገምቱት በላይ ረጅም ታሪክ እንዳለው አንዳንድ ድርሳናት ያሳያሉ። ለምሳሌ በ14ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈው የአጼ አምደጽዮን (1314-44) ዜና መዕዋል፤ በዚያ ዘመን ጫት በኢትዮጵያ ስለመቃሙና አንዳንድ የማሕብረሰብ ክፍሎች ተክሉን ያበቅሉ እንደነበር ያትታል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በርካታ በሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጫትን አዘውትሮ የመቃም ባህሪ ተስፋፍቶና ተንሰራፍቶ ይገኛል።

የጫት ተጠቃሚዎች ስለምን በዚህ ተክል ፍቅር እንደወደቁ የሚሰጡት ምላሽ የተለያየ ነው። አንዳንዶች እንቅልፍና ድብርትን በማባረር ነቃ የማለት ስሜት ይፈጥርልናል ይላሉ። ይህ ደግሞ ጫት በውስጡ ከያዛቸው ካቲኖንና ካቲን ከተባሉ አነቃቂ ንጥረ ነገሮች የመነጨ እንደሆነ ይገመታል። አንዳንዶች ደግሞ ለመዝናናት፣ ጊዜ ለማሳለፍና መቃሙ የሚፈጥረውን የጨረፍታ የደስታ ስሜት ለማጣጣም ነው ይላሉ። ከዚህ አልፎም ጫት ጉንፋንን፣ ተቅማጥንና ሌሎችም የሕመም ስሜቶችን ለመዋጋት እንደሚጠቅም የሚያምኑ አሉ። እንደ ሀረርጌ ባሉ አካባቢዎች የሚገኙ ጫት አብቃይ ገበሬዎች ጫት እየቃሙ ወይንም ከቃሙ በኋላ ወደ ሥራ መሰማራት ሥራ ከማሳለጡም በላይ የግብርና ሥራውን አሠልቺነትና ድካም ይቀንሳል ተብሎ ይታሰባል። ጫት መቃም የሚያዘወትሩ የጭነት መኪና አሽከርካሪዎች፣ የኮሌጅ ተማሪዎችና በጥበቃ ሥራ የተሠማሩ ግለሰቦች ደግሞ ጫት መቃም እንቅልፍ የማባረሪያ አይነተኛ መሣሪያ እንደሆነ ያምናሉ።

በሌላ በኩል የጫት ተጠቃሚ መሆን የስነ-አካላዊ (physiological) ብቻ ሳይሆን የስነ-አዕምሯዊ (psychological) ችግሮች መንስዔም እንደሆነና ለተለያዩ የጤና ችግሮች ሊያጋልጥ እንደሚችል በሰፊው ምርምር የተደረገበትና የተፃፈበት ጉዳይ ነው። ይልቁንም በተለይ በአሁኑ ወቅት የጫት ንግድ ዋና ከሚባሉ የሀገሪቱ የውጪ ምንዛሪ ምንጮች ተርታ መግባቱ፣ ባለፉት አራት አሥርተ ዓመታት በጫት አምራች ገበሬዎች ህይወት ላይ የሚታየው ተጨባጭ የኑሮ ለውጥና እንዲሁም በጫት አምራች ዞኖችና ክልሎች ከጫት ንግድ የሚገኘው ገቢ የብዙ ቤተሰቦች መተዳደሪያ መሆኑ እንዳለ ሆኖ የዚህ ተክል አመራረትና አጠቃቀም ምን ይመስላል? የገበያ ትስስሩ ምን መልክ አለው? በተለይ ደግሞ በዚሁ የገበያ ሠንሠለት ላይ በተለያየ ደረጃ የሚሳተፉ ሕጻናትና ወጣቶች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ በትምህርታቸው ላይ ምን አንድምታ አለው? ምንስ አይነት ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል? የሚሉትን ጉዳዮች መዳሰስና ባጠቃላይ የዚህ የገበያ ተክል የወደፊት ዕጣ ፈንታን በተመለከተ የመንግስት ፖሊሲና አቅጣጫ ምን መምሰል እንዳለበት መጠቆም ተገቢ ይሆናል።

## 2. የጥናቱ ዘዴዎችና የተመረጡ አካባቢዎች

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ከጫት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች መንስዔ ለማወቅና የመፍትሔ ኃሳቦች ለመሰነዘር የሚያስችል አቢይ የጥናት ፕሮጀክት ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ሲተገበር ቆይቷል። የዚህ አቢይ ፕሮጀክት አካል የሆነው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጫት ንግድ ሥራ ላይ

የሕጻናትን ተሳትፎና በዚያም ተሳትፎ ምክንያትነት በሕጻናቱ ትምህርት ላይ የሚያጋጥሙ መሰናክሎችና በአጠቃላይ የሚደርስባቸውን የስነ-ልቦናና የጤና ችግሮች መመርመርና የመፍትሔ ኃሳቦች መሰንዘር ነው።

የጥናቱ የትኩረት ቦታዎች በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ሀረርጌ ዞን የምትገኘው የአወዳይ ከተማና አካባቢዋ፤ እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሠቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በሲዳማ ዞን ውስጥ የምትገኘው የጩኮ ከተማና የወንዶ ገነት አካባቢ ናቸው። ሁለቱ ከተሞች የተመረጡበት ምክንያት ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት የጫት አምራች፤ መሸጫና ማሰናጃ ከተሞች ሁሉ ከፍተኛ የጫት ንግድ እንቅስቃሴ የሚደረገባቸውና ከሌሎቹ ሁሉ የላቁ መሆናቸው ስለታወቀ ነው።



የጥናቱ ዘዬ ድብልቅ ዘዴዎች (Mixed Methods) የሚባለው ሲሆን፤ ሁለቱንም የታወቁ የመረጃ አሰባሰብ መንገዶችን ማለትም አይነታዊ (Qualitative) እና አኃዛዊ (Quantitative) መረጃዎችን በማፈራረቅ እንደ አስፈላጊነቱ በሳይንሳዊ መንገድ በማቀናጀትም ተጠቅሟል። ሁሉም ዓይነት መረጃዎች የተሰበሰቡት ወደ ተጠቀሱት ከተሞችና አካባቢያቸው ከህዳር 2008 ዓ.ም ጀምሮ የመስክ መረጃ ማሰባሰብ ሒደት ነው። ዓይነታዊ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በሁለቱም ከተማዎች ከሚኖሩ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች፤ የወረዳና የከተማ ባለስልጣናት፤ የጫት ነጋዴዎች፤ መምህራንና ቤተሰቦች፤ በተለይም በጫት ንግድ ሠንሠለቱ ውስጥ ከሚሳተፉ ሕጻናትና ወጣቶች ጋር በተናጠልና በጋራ በተደረጉ በርካታ ጥልቅ ውይይቶች ነው። አሀዛዊ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ደግሞ በሁለቱም ከተሞች ለሚኖሩ የጥናቱ ዓላማ በቀጥታ ለሚመለከታቸው በተለያየ ደረጃ በንግዱ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው 90 ሕፃናትና ወጣቶች መጠይቆችን እንዲሞሉ በማድረግ ነው። ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች ማኅደር ውስጥ የተገኙ የጽሁፍ መረጃዎችና የተመራማሪውን ምልከታም እንደግብዓት መጠቀምም ተችሏል።

3. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

ሀ) በአሁኑ ወቅት የዚህ ጥናት የትኩረት ቦታዎች በሆኑት የሀገሪቱ ሁለት የጫት ገበያና ማሰናጃ ማዕከላት በመካሄድ ላይ ያለው የጫት ንግድ የልጆችን በተለይም ዕድሜያቸው ለአካለ-ቅጥር (14 ዓመት) ያልደረሱ ለጋ ሕጻናትን ጉልበት የሚጠቀም መሆኑንና ይህም ሁኔታ የዓለም አቀፉ የስራ ድርጅት “አደገኛ” ብሎ ከሚፈርጃቸው የስራ ሁኔታዎች ጋር በእጅጉ የሚመሳሰልና ከሌሎች የሕጻናትን መብት ለመጠበቅና ለመንከባከብ ከተደነገጉ የሀገሪቱ ህጎች ጋር የሚጣረሱ ሆነው ተገኝተዋል።

ለ) እነዚህ በጫት ንግድ የስራ ሂደት በተለያዩ እርከኖች የሚሳተፉ ለጋ ሕጻናትና ሌሎችም ወጣቶች የሚሰሩት የስራ ዓይነት ጫትን ያማከለ እንደመሆኑ መጠን፤ ወጣቶቹ በዚያ ለጋ ዕድሜያቸው ወደ ጫት መቃም ሱስ የመሳብና የመጠመድ አደገኛ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ጥናቱ ያሳያል። በርካታ ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደሚያስገነዝቡት ደግሞ እንዲህ አይነት ሱሶች በተለይ በሕጻናትና በወጣቶች ላይ ሲከሰቱ በአካላዊና አዕምሯዊ ዕድገታቸው ላይ በዘላቂነት የሚያስከትሉት ጦስ እጅግ አደገኛ ነው።

ሐ) ጥናቱ እንደሚያሳየው በዚህ የንግድ ሰንሰለት ውስጥ የሚሳተፉ ሕጻናትና ወጣቶች የዕድሜ ስርጭት ትንሹ ስምንት ዓመት ሲሆን፤ አብዛኛዎቹ የሚገኙበት የዕድሜ ክልል ደግሞ ከ13-16 ዓመት ያለው ነው። ይህ ደግሞ የልጆች የትምህርት ዕድሜ ከሚባለው ዋናው ክፍል መሆኑ ይታወቃል። የዚህ ጥናት ዋና የምርምር ትኩረት ደግሞ የነዚህ ልጆች የትምህርት ሁኔታ ነበር። በዚህም መሠረት የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ ጫት ሠራተኛ የሆኑ ልጆች ስራውንም ትምህርቱንም ጎን ለጎን የሚያስኬዱ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ ደግሞ የቤተሰባቸውን ቀዬ ለቅቀው በጫት ማሰናጃ ከተማዎቹ ውስጥ የሚኖሩ በመሆኑ ጭራሹኑ ትምህርት የማይማሩ ሆነው ተገኝተዋል።

መ) ትምህርትና የጫት ንግድ ስራን ጎን ለጎን የሚያስኬዱትን በተመለከተ እነዚህ ልጆች ትምህርት ቤት መሄዳቸውን ባያቋርጡም፤ የሚሳተፉበት የጫት ንግድ ሥራ ሁኔታና የስራው ሰዓት ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል ከፍተኛ ችግር እንደሚፈጥርባቸውና በውጤታቸውም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው ጥናቱ አመልክቷል። በሁለቱም የጥናቱ አካባቢዎች ዋናው የጫት ግብይትና መሰናዶ ስራ የሚሰራው ሌሊቱን ሙሉ በመሆኑ እነዚህ ሕጻናት በዚያ ሰዓት እንደ ሌሎች የዕድሜ እኩዮቻቸው ከመተኛትና ከማረፍ ይልቅ በስራ ላይ በመሆናቸው ጠዋት አርፍደው ወደ

ትምህርት ቤት ይገባሉ፤ የከሰዓት በኋላ ፈረቃ ሲሆኑ ደግሞ በጫት ስራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት ሲሉ ቀደም ብለው ትምህርታቸውን አቋርጠው ከትምህርት ቤት ግቢ ይወጣሉ። በትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥም ቢሆን በእንቅልፍ እጥረት ምክንያት ብዙውን ሰዓት በማዛጋትና በማንጎላጀት የሚሰጠውን ትምህርት በአትኩሮት ለመከታተል ይቸገራሉ። በዚሁም የስራና የእንቅልፍ ጫና ምክንያት ሁለት ወይም ሶስት ቀን ከትምህርት ቤት መቅረት በነዚህ ልጆች አካባቢ የተለመደ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል። ከዚሁ በቂ ሰዓት/ጊዜ ከማጣት ጋር ተያይዞ የቤት ስራዎችን ለመስራት፤ ለንባብና ለጥናት የሚሆን የጊዜ እጥረት ስላለባቸው ከሌሎች መደበኛ ተማሪዎች ጋር ተወዳዳሪና ውጤታማ ለመሆን እንደሚቸገሩም ታይቷል ።

ሠ) ሌሎቹ ጨርሶውኑ ትምህርት ቤት የማይሄዱት ሕጻናት ሠራተኞች ደግሞ ራቅ ካሉ አካባቢዎች ወደ ተጠቀሱት ከተሞች የመጡና ከቤተሰባቸው ርቀው በጫት ንግድ ሥራ (ያውም አብዛኞቹ ብዙም ክፍያ በማስያስገኙ እንደ ሸክምና ጽዳት በመሳሰሉ ስራዎች) ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል። ከሁሉም በላይ እነዚህ ሕጻናት ከትምህርት መገለል ብቻ ሳይሆን የኑሮ ሁኔታቸውና ደህንነታቸው፤ እንዲያም ሲል የወደፊት ተስፋቸው አጅግ አሳሳቢ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል። በተለይም በወንዶ ገንት- ጩኮ የሚገኙት እነዚህ ለፍቶ-አደር ሕጻናት እንደ ዕድሜያቸው ለጋነት የቤተሰብ ድጋፍና ጥበቃ አያገኙም። አነስተኛ ተከፋይ ሥራዎችን ከመስራታቸው አንጻር ገቢያቸው የማያወላዳ በመሆኑ በበቂ አይመገቡም፤ በአግባቡ አይለብሱም፤ በአንድ ክፍል ውስጥ ከ20-30 የሚሆኑት በአንድ ላይ ታጭቀው የሚያድሩ በመሆኑ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎችና የጤና ችግሮች የተጋለጡ ናቸው። ከዚህም አልፎ እነዚያ ማደሪያዎች ለአንድ ሰው በቀን 3 ብር የሚያስከፍሉ ናቸውና ይህንን ክፍያ መክፈል ያልቻሉት ሕጻናት በጅምር ቤት ውስጥ ለማደር በመገደዳቸው በአራዊት አስከመበላት የደረሱ መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል።

## 4. የፖሊሲ አቅጣጫና የመፍትሔ ኃሳብ

ሀ) ጫት በራሱ እጅግ አወዛጋቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አገራችን ቁርጥ ያለ የወደፊት አቅጣጫና አቋምን የሚያመለክት ሕግም ሆነ የፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና መተግበር ላይ አልደረሰችም። ኢትዮጵያ ምንም እንኩዋን በጫት ምርትም ሆነ ፍጆታ በዓለም ቀዳሚ ከሆኑት ሀገሮች ተርታ የምትመድብ ብትሆንም የጫት አመራረት፤ የንግድ ሥርዓትና አጠቃቀምን የተመለከተ ደምብም ሆነ ፖሊሲ ያለመኖር ክፍተት ለረጅም ጊዜ የዘለቀና አሁንም ያልተደፈነ ቀዳዳ ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ ሕጻናት፤ በተለይ በጫት ንግድ ስራ ላይ ሊኖራቸው የሚገባው የተሳትፎ ደረጃና መጠን እስከምን ድረስ መሆን እንዳለበት ታስቦበት የተዘጋጀ መመሪያም ሆነ ደንብ ይኖረናል ተብሎ አይጠበቅም። ስለሆነም ጫትን በተመለከተ በውል የተመከረበትና የሰከነ ሀገራዊ የፖሊሲ ማዕቀፍና ደምብ ማዘጋጀት ቀዳሚው እርምጃ መሆን ይገባዋል።

ለ) ይህን ማድረግ ከተቻለ ሕጻናቱ በጫት ዙሪያ የሚኖራቸው የስራ ተሳትፎ ምን መምሰል እንዳለበት መመሪያ፤ ወይም ሕግና ስርዓት ወደማበጀት መሸጋገር ይቻላል። ያም ሆኖ ግን እንደ አጠቃላዩ የጫት ፖሊሲ ሁሉ የሕጻናቱም ጉዳይ አንድ ዕልባት ላይ ከመድረሱ በፊት ብዙ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠይቃል። ለምሳሌ በዚሁ ጥናት ከተዳሰሱ ውስብስብ ጉዳዮች ውስጥ፤ እንደ ብዙ የአፍሪካ ማሕበረሰቦች ሁሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦችም በልጆች ስራ የሚገኝ ገቢን እንደመተዳደሪያ የመጠቀማቸው ጉዳይና ከሁሉም በላይ ደግሞ በብዙ የአፍሪካ ባሕሎች ውስጥ የልጆች በስራ ላይ መሳተፍ ከመኮነን ይልቅ ከማሕበረሰባቸው አኗኗርና ሌሎች ዕሴቶች ጋር የመተዋወቂያና የመዋኃጃ መንገድ ተደርጎ መታየቱ አጽንዖት ሊሰጠው ይገባል። ይሁንና የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት ሕጻናት የስራ መስክና የስራ ሁኔታ በባሕሪው የተለየና በሕጻናቱ አዕምሯዊና አካላዊ ዕድገት እንዲሁም የወደፊት ኑሮ ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊጋርጥ የሚችል በመሆኑ አንዳንድ ወሳኝና አስቸኳይ እርምጃዎች መወሰድ እንደሚኖርባቸው ሊሰመርበት ይገባል።

ሐ) አሁን ባለው ሁኔታ የሕጻናትን የቅጥር ሥራ ቁርጥ አድርጎ በሕግ ማገድና የልጆችን ጉልበት ከኢኮኖሚው ጠራርጎ ማስወጣት ሊሉት እንጂ ሊፈጽሙት የሚከብድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የልጆችን ጤናና ትምህርት አደጋ ላይ የሚጥል አሰራርን እጃችንን አጣጥፈን ከመመልከት በትንሹ እንኳን ሕጻናትን የሚመለከቱ መሠረታዊ ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎችንና ሀገራዊ ሕጎች በአግባቡ መከበራቸውን መከታታልና ማስፈጸም ጥሩ መነሻ ይሆናል። ለምሳሌ በኢትዮጵያ የሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/2003 መሠረት በሀገሪቱ ለአንድ ልጅ የቅጥር ስራን የመጀመሪያ ዕድሜ 14 ዓመት በመሆኑ ከዚህ ውጪ የሆነ አሰራር ሁሉ ሕገ-ወጥ ነውና ማስቆም ያስፈልጋል።

መ) በቅድሚያ 14 ዓመት የአቅመ-ቅጥር መጀመሪያ ዕድሜ መሆኑን በቂ ግንዛቤ ካገኘ በኋላ በተለይ ጫትን በሰፊው በሚያመርቱና በሚነግዱ አካባቢዎች ለሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሕጻናት በለጋ ዕድሜ በጫት ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት በትምህርታቸውም ሆነ በጤንነታቸው ላይ የሚስከትለውን አደጋ ደጋግሞ ማስተማርና ማሳወቅ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባና ቶሎ መጀመር ያለበት ተግባር ነው።

ሠ) ከጥናቱ በተገኘው መረጃ መሠረት ለብዙዎቹ ሕጻናት በጫት ንግድ ሥራ ላይ መሳተፍ አንዱ ምክንያት

የወላጆች ግፊት፣ ማለትም ወላጆች በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች ሕጻናት ልጆቻቸውን ወደ ጫት ንግድና ተዛማጅ ስራዎች እንዲገቡ ማበረታታቸውና መገፋፋታቸው ስለሆነ የማስተማርና የማሳሰብ ስራ መሰራት ይኖርበታል:: ስለዚህ ጫት በሰፊው በሚመረትባቸው አካባቢዎች በሚዘጋጁ መድረኮች ትምህርት መስጠት፣ ውይይቶችን ማድረግና ኃሳቦች እንዲንሸራሸሩ



ማድረግ ወላጆች ያሉትን ጎጂ አዝማሚያዎች ተረድተው በልጆቻቸው ላይ ባለማወቅ ከሚያደርሱት ተጽዕኖ እንዲታቀቡ ይረዳል::

ረ) በነዚህ መድረኮች በተቻለ መጠን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግስትና የከተማ አስተዳደር ባለስልጣናት፣ የትምህርት ቢሮ ሠራተኞች፣ ወላጆች፣ መምህራን፣ የጫት ነጋዴዎችንና እንዲሁም ገበሬዎችን ማሳተፍ ያስፈልጋል::

ሰ) እነዚህ ትምህርታዊ መድረኮች ተጠሪ ባለቤትና አስተባባሪ እንዲኖራቸው በማድረግ ትምህርቱ በማሕበረሰቡ ውስጥ በአግባቡ እንዲሰርጽ በሚረዱ ተከታታይነት ባላቸው ክንውኖች ማስኬድ ያስፈልጋል:: የእነዚህ መድረኮች ተግባርና አፈጻጸም ስኬታማ ይሆን ዘንድ የሲቪል ማኅበራት ድጋፍና ተሳትፎ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ወሳኝም ነው::

ሸ) በዚህ ጥናት እንደተረጋገጠው በጫት ንግድ ሥራ ሂደት ውስጥ የጉልበት ሥራ በመስራት ላይ የተሰማሩ ራቅ ካሉ አካባቢዎች የሚመጡ ዕድሜያቸው እስከ ስምንት ዓመት ዝቅ ያለ ሕጻናት ይገኛሉ:: በአሁኑ ወቅት ችግሩ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ለመድረሱ በርካታ ጠቋሚ ነገሮች ይታያሉ:: ሕጻናቱ ከትምህርታቸው ተስተጓጉለው በበሽታና በችግር ይጠቃሉ፣ በልጅነታቸው ለተለያዩ ሱሶች ይጋለጣሉ፣ ለተለያዩ ወንጀሎችና ለወንጀለኝነትም የተጋለጡ ናቸው:: እንግዲህ ችግሩ በቶሎ መቀጨት ያለበት መሆኑ ብዙም አያወያይም:: እንደ አማራጭ የመፍትሔ ኃሳብ ግን ከዚህ በፊት በአካባቢው ባለስልጣናት ተሞክሮ ውጤታማ ያልሆነውን ሕጻናቱን ወደየመጡበት አካባቢዎች የመመለስ ሙከራ አንዱ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ይህ ሰፊ ስራና ውይይት የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ያለፈውን ሙከራ ችግሮች ነቅሶ በማውጣትና ትምህርት በመውሰድ በዚያ ላይ መገንባት ጠቃሚ አካሄድ ሊሆን ይችላል::

ግርማ ነጋሽ

ምንጭ፡- Girma Negash "***The Education of Children Entangled in Khat Trade in Ethiopia: The Case of Two Khat Market Centers***" FSS Research Monograph No. 13. 2017

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሠነድ የታተመው ከሲቪል ሶሳይቲ ድጋፍ ፕሮግራም (CSSP) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው:: ለሠነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የተመራማሪው ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሽ ድርጅቱን ወይም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን አቋም እንደሚያንጸባርቅ ተደርጎ መወሰድ የለበትም::

§§ አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) §§ ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

§§ ስልክ፡- 0116 29 78 88/91 §§ ፋክስ፡- 0116 29 78 89 §§ ኢሜል፡- fss@ethionet.et §§ ድረ-ገጽ፡- www.fssethiopia.org